

# የዶሮ አረባብ ዘዴዎች ተግባራዊ መመሪያ

SOS SAHEL
ETHIOPIA

Irish Aid
Department of Foreign Affairs
An Roinn Gnóthaí Eachtracha

# መግቢያ

በአገራችን የዶሮ እርባታ ተግባር ጥንታዊ የእርሻ ስራ ቢሆንም ከኋላ ቀር አረባብ፤አመጋገብ፤ አያያዝና ጤና አጠባበቅ ባለመላቀቁ ከዘርፉ የሚገኘው ጠቀሜታ አነስተኛ ሆኖ ይገኛል፡፡ በሀዋሳ ተፋሰስ አካባቢ በተደረገ ጥናት ከህዝብ ብዛት መነሻ የመሬት ይዞታ ጥበት የሚስተዋልበት በመሆኑ የዶሮ እርባታ ስራ ደግሞ በአነስተኛ ቦታና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አርሶ አደሮችና አርቢዎች መከናወን የሚችል ስለሆነ የምግብ እጥረት በተለይም ጎልቶ የሚታየውን ፕሮቲን እጥረት በመቅረፍ፤ የምግብ ዋስትናንም ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት የሚጫወተው ሚና ቀላል አይደለም ፤ ዶሮዎች ከመባዛት ባህሪያቸው አንጻር በህይወት ዘመናቸው የሚሰጡት ምርት ከሌሎች የእርባታ ስራዎች የተሻለ ሆኖ ይገኛል፡፡ ከዚህ አንጻር በእርባታው ስራ የሚታዩ ጉድለቶችን በማስወገድ ከልማዳዊው አሰራር ወደ ተሻሻለ የአረባብ ዘዴ በማሸጋገር አርቢውን ህብረተሰብ ከምርቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ይህ የዶሮ አረባብ ዘዴ መመሪያ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

# የዶሮ አረባብና አያያዝ

የዶሮ እርባታ ተግባር በአግባቡ ለማከናወን መሰረታዊ የሆኑ የአረባብና አያያዝ ዘዴዎችን መረዳት አስፈላጊ ይሆናል፤ ከነዚህም ውስጥ ዶሮዎች ዝርያ፤ ዶሮ ቤት አሰራርና ቁሰቁስ፤ የዶሮ መኖና አመጋገብ ፤ የጫጩት ማሳደግ ዘዴ፤ እንቁላል ጣይ ዶሮዎች አረባብና እንቁላል ማስፈልፈል፤ የዶሮ በሽታና ባዮሴኩሪቲ ይገኙበታል፡፡

## የዶሮዎች ዝርያ

ዶሮዎች እንደሚሰጡት ምርት ዓይነትና ብዛት/ክብደት/ የእንቁላል፤የስጋ ፤ የእንቁላልና የስጋ/ dual-purpose/ በመባል ይለያሉ፤የእንቁላል ዝርያዎች የሰውነት ክብደታቸው አነስተኛ ሲሆን ከፍተኛ የእንቁላል ምርት ይሰጣሉ፤የሚመገቡትን መኖ በአብዛኛው ወደ እንቁላል ምርት የመቀየር ባህሪ አላቸው፤ የእንቁላል ጣይ ዝርያነት ከሆኑት ኋይት ሌግሆርን white leg horn ዶሮዎች ታዋቂ ሲሆኑ እናት ዶሮዎች ክብደት 2ኪሎ ግራም፤አውራው 2.7 ኪሎ ግራም ይመዝናል፤ዓመታዊ እንቁላል ምርታቸው 300 እንቁላል በላይ ነው፡፡ ከነዚህ ዶሮዎች የተዳቀሉ በርካታ ዶሮዎች Bovans brown, Bovans white, Isa brown ወደ አገራችን ገብተው ይራባሉ፡፡





የሥጋ ዶሮዎች የሚመገቡትን መኖ በአብዛኛው ወደ ስጋ ምርት የመለወጥ ባህሪ ያላቸው ሆኖ የመኖ ፍጆታቸውም ከፍተኛ ነው፤ ከ2 ወራት ባነሰ ጊዜ ለእርድ/ 2 ኪሎ ግራም/ ይደርሳሉ፤ የእንቁላልና የስጋ ቅይጥ ባህሪ የያዙት ደግሞ መካከለኛ ምርት የሚሰጡ ሲሆን ወደ አገራችን ከገቡት ሮድ አይስላንድ ሬድ /Rhode island Red/ ይገኙበታል፤ የእንቁላል ምርታቸው በአመት 230 ያህል ነው፡፡

## የዶሮ ቤት አሰራርና ቁሳቁስ

የዶሮ እርባታ ተግባር ውጤታማ ለማድረግ ጤናማ አካባቢን ማመቻቸት የሚያስፈልግ ሲሆን እንደ ሚረቡት ዶሮዎች ብዛት የዶሮ ቤት ማዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል፤ የዶሮ ቤት ሲሰራ በተቻለ መጠን ከመኖሪያ አካባቢ በመራቅ የሰውና የእንስሳት ንክኪን መቀነስ፤ ቦታውም ተዳፋትነት ያለው ሆኖ ለውሀ መርጋትና ለጀርም መራባት የማያመች እንዲሁም የመብራት የውሀ የመንገድ ቅርበትና አመችነት ከግምት ውስጥ የሚገቡ ይሆናል፡፡ የዶሮ ቤት ሲሰራ ለአየር እንቅስቃሴ ሲባል በሁለት ጎን ከፊል ግድግዳው ክፍተት ያለው ሆኖ የጸሀይ ብርሀንም ቀጥታ ዶሮዎች ላይ በማያርፍ መልኩ ተደርጎ መሰራት አለበት፤ የዶሮ ቤት ወለሉ በኩስና በፍሳሽ እንዳይረጥብ ጉዝጓዝ/ሳጋቱራ፤ጭድ፤ገለባ/ መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡እናት ዶሮዎችን በካሬሜትር 5 ያህል፤ቄብ ዶሮዎችን ደግሞ 10-12 በመያዝ ማርባት ይቻላል፡፡

## የዶሮ ቤት ቁሳቁስ

ቁሳቁሶች ከፕላስቲክና ከብረት የሚሰሩ ሲሆን ለአነስተኛ እርባታዎች በአካባቢ ቁሳቁሶች ከእንጨትና ከሸክላም ማዘጋጀት ወጪን ይቆጥባል፤ ከቁሳቁሶች ውስጥ የጫጩት ማሞቂያ፤መመገቢያ፤የውሀ መጠጫ፤እንቁላል መጣያ ጎጆ ፤ባልዲዎች ፤አካፋ ፤ጫጩት መከለያና የእቃ ማጠቢያ እቃዎች ይገኙበታል፤
የጫጩት ማሞቂያዎች በተፈጥሮ በእናት ዶሮ ምትክ በርካታ ጫጩቶችን በሰው ሰራሽ ዘዴ ለማሳደግ የሚረዳ ሲሆን በአብዛኛው የኤሌክትሪክ ሀይል በመጠቀም የሚከናወን ነው፤ ለዚህ ተግባር አምፖሎች፤ ሬዚስተር፤ ዘመናዊ ማሞቂያዎች ግልጋሎት የሚሰጡ

ሲሆን መብራት ሲቋረጥ ጀነሬተርና ለአነስተኛ እርባታዎች ከሰል ግልጋሎት ላይ ይውላል፡፡ የኤሌክትሪክ ሀይል በሌለበት አካባቢ የገለባ ሳጥን በመጠቀም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው /እስከ 70/ ጫጩቶችን ማሳደግ ይቻላል፡፡





የዶሮ መመገቢያዎች  የዶሮ ውሀ መጠጫ

## የዶሮ መኖና አመጋገብ

ዶሮዎች ሰውነታቸውን ለመጠበቅ፤ለማንቀሳቀስ፣ ለማደግ ፤ለምርት፣ ከበሽታ ለመከላከልና ለሰውነታቸው ሙቀት ለማመንጨት መኖ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ዶሮዎች ከሌሎች እነስሳት የሚለዩበት የማያመነዥሁ፤ ከንፈርና ጥርስ የሌላቸው መሆኑ፣የዕድገት መጠናቸው ፈጣን መሆን/የሥጋ ዶሮዎች ከ2 ወራት ባነሰ ጊዜ 30 እጥፍ ያህል ያድጋሉ/፤ ሲፈለፈሉ ከ40-50 ግራም የሚመዝኑ በ2 ወራቸው 1.5--2

ኪ.ግ ይመዝናሉ፣ሣርና የቃጫነት ይዘት ያላቸውን የመኖ ጥሬ ዕቃዎች በብዛት መመገብ አይችሉም፡፡ የአፈጣጠር ሁኔታቸው ከአመንዣኪ እንስሳት በተሻለ የተሟላና የተመጣጠነ መኖ /በቫይታሚን፣ በፕሮቲን (essential & non-essential amino acid ) ፤ከፍልፋዮችና በመሳሰሉት/ አቅርቦትን ይፈልጋል ፡፡

የዶሮ መኖ ንጥረ ነገር ለሰውነታቸው የሚሠጠውን ጥቅም በማየት ኬሚካል ይዘታቸውንና ባህሪያቸውን መነሻ በማድረግ ኃይል ሠጪ፣ ገንቢ መኖ፤ ቫይታሚን፤ማእድናት፤ውሀ በመባል ይመደባሉ፡፡

**ኃይል ሰጪ** ፤ንጥረ ነገር ለዶሮዎች ጤናማ የሰውነት አሠራርና ምርት አስፈላጊ ይሆናል፤ ኃይል ሰጪ በአብዛኛው በጥራጥሬ ውስጥ ይገኛሉ፤በቆሎ፤ስንዴና ስንዴ ተረፈ ምርቶች፤ገብስ ማሽላ በሀይል ሰጪነት ይታወቃሉ፤ሆኖም የፕሮቲን ይዘታቸው አነስተኛ ስለሆነ ከነዚህ ብቻ የተሟላ መኖ ማዘጋጀት ያዳግታል፤

**ገንቢ መኖ**፤ ስጋና እንቁላል ለሰው ምግብነት በገንቢነታቸው ይታወቃሉ፤ ለዶሮዎች የገንቢ ንጥረ ነገር ለእድገት፣ ለዕንቁላል ምርት፣ ለጤናማ ዕድገት ያስፈልጋል፤ የገንቢ ንጥረ ምግብ ይዘት ያላቸው ጥሬ ዕቃዎች ከእፅዋት እና ከእንስሳት ውጤቶች ማግኘት የሚቻል ሲሆን አኩሪአተር፤ የዘይት ጭማቂዎች/የኑግ ፤የሰሊጥ፤ የኦቾሎኒ፤ጎመን ዘር../ ቦሎቄ፤ከእንስሳት ምርት ወጤቶች የተፈጨ ስጋና አጥንት/ከተረፈ ምርት/፤ዓሳ መኖ፤ ደም መኖ ጥሩ የፕሮቲን ምንጭ ናቸው፤ የፕሮቲን ክፍልፋዮች የሆኑ /ላይሲን ሜቲዮኒን/ በተጨማሪነት ከመኖ ጋር የሚቀየጡ ገበያ ላይ ይገኛሉ፡፡

**ቫይታሚን** ፤ለጤናማ የሰውነት አሰራር፤ለምግብ ውህደት ለኢንዛየሞች አሰራር፤በአጠቃላይ አግባብ ላለው ምርት ያስፈልጋሉ፤ ቫይታሚን ኤ-ለእድገት ለመራባት ለአይንና ለውስጥ አካላት ጤንነት አስፈላጊ ነው፡፡አረንጓዴ ቅጠላቅጠሎች /በተለይም

ሺፈራው፤አልፋአልፋ/ ቢጫ በቆሎ በጥሩ ምንጭነት ይታወቃሉ፡፡ ቫይታሚን ቢ/B1,B2,B6,B12/ በኢንዛየሞች ይዘት፤በምግብ ውህደት፤በነርቮች አሰራር፤በምርት ውጤት ላይ ሚና ይጫወታሉ፤በጥራጥሬ በቅጠላቅጠል ፤በእንስሳት ምርት ውጤት ይገኛሉ፡፡ቫይታሚን ዲ ለአጥንትና ለእንቁላል ቅርፊት አስፈላጊ ሲሆን የጸሀይ ብርሀን ርካሹ ምንጭ ነዉ፤ቫይታሚን ኢ፤ኬ፤ሲ፤ፎሊክ አሲድ፤ኒያሲን፤ፓንቶቴኒክ አሲድ በአብዛኛው በመኖ ጥሬእቃዎችና ቅጠላቅጠል ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡

**ማእድናት**፤ ለሰውነት አካልና ለኢንዛየም አፈጣጠርና አሰራር አስፈላጊ ሲሆኑ፤ዋና/Macro/ ጥቃቅን /micro/ በመባል ይከፈላሉ፤ዋና የሚባሉት ካልስየም ለአጥንት ለህዋሳት ለነርቭ ስርአት ለእንቁላል ቅርፊት አስፈላጊ ሲሆኑ የኖራ አፈርና የተፈጨ አጥንት ዳይ ካልሲየም ፎስፌት ጥሩ ይዘት አላቸው፤ፎስፎረስ ለአጥንትና ለመኖ ውህደት ለደም አሰራር የሚያስፈልግ ሆኖ ዳይ ካልሲየም ፎስፌት የተፈጨ አጥንት ፉርሽካም በምንጭነት ይታወቃሉ፤ማግኒዝየም በአጥንት በህዋሳት ኢንዛየሞች አሰራር ላይ ሚና ያለውና በጥራጥሬና ዘይት ጭማቂዎች ውስጥ የሚገኝ ነው፤ፖታሲየም ለነርቭ ስርአትለምግብ ውህደት ለእድገት የሚረዳ ሆኖ ቅጠላቅጠሎች ውስጥ ይገኛል፤ሶዲየም በሰውነት ፈሳሾች ለእድገትና ምርት፤ክሎሪን ለምግብ ፍላጎትና እድገት የሚያስፈልጉ ሲሆን የሁለቱም ምንጭ ጨው ነው፡፡



ዘመናዊ ቁሳቁስ በመጠቀም ያደጉ ጫጩቶች/ 42 ቀናት እድሜ/

## መኖ አቀያየጥና አመጋገብ ፤

መኖ ሲቀየጥ የዶሮዎች እድሜ፤ዝርያ፤የመኖ ጥሬ እቃ ይዘት ከግምት ውስጥ ይገባሉ፤ጥራጥሬና ተረፈ ምርቶች በየአካባቢው የሚገኙ ሲሆን ገንቢ መኖና ቫታሚን ማእድናት የግንዛቤ ጭምር እጥረት  እንዳለ መገንዘብ ይቻላል፡፡
ለእንቁላል ጣይ ዶሮ ጫጩቶች በመጀመሪያው ሳምንት 12 ግራም ለአንድ ጫጩት፤ በአራተኛው ሳምንት 31 ግራም፤በ8ኛው 47 ግራም፤በ12ኛው 63ግራም ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ጥናቶች ይጠቁማሉ፤ለእናቲቶች ከ110-150 ግራም የተመጣጠነ መኖ የሚስፈልግ ሲሆን እንቁላል መጣል የጀመሩ እሰከ 35 ሳምንት እድሜያቸው ምርታቸው እየጨመረ ስለሚሄድ በቂ አቅርቦት ያስፈልጋል፡፡ በመኖ አመጋገብ ተቀይጦ ከ15 ቀናት በላይ ያልቆየ /ትኩስ/ መኖ ማቅረቡ  ተመራጭ ነዉ፤ በቆይታ ቫይታሚኖች ይዘት የሚጎዳና የመሻገት ሁኔታም ሊጀምር ይችላል፤በአቀማመጥም ወቅት የአየር እንቅስቃሴ በሚኖር መልኩ ተደርድሮ እርጥበት ነቀዝና አይጥ በመከላከል እንዲሁም የኬሻዎች ዝውውር በሽታ እንዳያስከትል ንጽህናውን መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡

ዕንቁላል ማስፈልፈል

በተፈጥሮ የአገራችን ዶሮዎች እንቁላል በመታቀፍ ሙቀት በመስጠትና ምቹ ሁኔታን በመፍጠር/ እንቁላሉን በመገልበጥና በማገላበጥ/ ጫጩት እንዲፈለፈል ያደርጋሉ፤በዘመናዊ አሰራርም መሳሪያዎችን በመጠቀም በርካታ እንቁላል ማሳቀፍና

ማስፈልፈል/ከ50 እንቁላል ጀምሮ 100 000 ያህል በሚታቀፉ መሳሪያዎች/ ይከናወናል፤መሳሪያዎች አጠቃቀም ላይ ትኩረት የሚሹ ፤የሙቀት መጠን የአየር እርጥበት / relative humidity/ የእንቁላል መገልበጥ የአየር እንቅስቃሴን ማመቻቸት ዋነኞቹ ናቸው፡፡በእንቁላል ማስፈልፈል ተግባር ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩት በሽታ፤የእናቲቶች አመጋገብና እድሜ ፤የእንቁላል አሰባሰብና አቀማመጥ፤ የመሳሪያዎች ሙቀትና አሰራር መዛባት፤የአውራና የእናት ቁጥር መመጣጠንና ዝምድና የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የጫጩት ማሳደግ ዘዴዎች

ሀ) በተፈጥሮ ማሳደግ

ይህ በአብዛኛው የሀገራችን የገጠሩ ህብረተሰብ የአካባቢ ዝሪያ ዶሮዎችን ለማርባት የሚጠቀምበት የአስተዳደግ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ጭር የማለት ጠንካራ ባህሪ ያላቸው የሀገር ዝሪያ ዶሮዎች በመጠቀም እንቁላሎቹ ከተፈለፈሉ በኋላ ጫጩቶቻቸው የሚፈልጉትን ሙቀትና ሌላውን እንክብካቤ ራሳቸው በመስጠት ያሳድጋሉ፡፡የዚህ ዓይነቱ የጫጩት አስተዳደግ ዘዴ በበሽታና በአውሬ ጥቃት ምክንያት የጫጩቶች ሞት እጅግ በጣም ከፍተኛ ስለሆነ/ የሞት መጠን 60 በመቶ/ ይደርሳል ፡፡ በዚህም የተነሳ ከዘርፉ የሚጠበቀዉን ምርት ማግኘት አልተቻለም፡፡

ለ) በሰው ሰራሽ ዘዴ ማሳደግ

በሰው ሰራሽ ማሳደጊያ ዘዴዎች በአንድ ጊዜ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ጫጩቶች ለማሳደግና የተመጣጠነ እድገት ያላቸውን ጫጩቶችን ለማግኘት ይረዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጫጩቶቹ በቀላሉ ለአውሬና ለበሽታ ጥቃት አይጋለጡም፡፡ ለዚህ ተግባር የኤሌክትሪካ ማሞቂያዎች /ባለ 100-200 ዋት አምፖሎች ፤ሬዚስተሮች፤ዘመናዊ ማሞቂያዎች /ግልጋሎት የሚሰጡ ሆኖ መብራት ሲቋረጥ ጀነሬተርና ከሰል ጥቅም ላይ ይውላል፤ጫጩቶች በመጀመሪያው ሳምንት 35 ድግሪ ሴንትግሬድ ወደ

ወራቸው አካባቢ 25 ድግሪ ሴንትግሬድ ያህል ሙቀት ያስፈልጋቸዋል፤
ኤሌክትሪክ በሌለባቸው አካባቢዎች በሙቀት አልባ ገለባ ሳጥን/ Hay-box brooder/ የማሳደግ ዘዴ አነስተኛ ቁጥር ጫጩቶችን ከ20-70/ ጣዉላ፤ ወንፊት ሺቦና ጭድ በመጠቀም ጫጩቶቹ በራሳቸው ሙቀት እርስ በርስ ተሟሙቀው የሚያድጉበት ሲሆን የጫጩት ማሰደጊያ ሳጥኖች የመዋያና የማሞቂያ/የማደሪያ/ አላቸው፡፡
ዕንቁላል ጣይ ዶሮዎች አያያዝ፤ አግባብ ያለው ጤናማ ምርት ለማምረት ከጫጩትነት እድሜ ጀምሮ ያለው እንክብካቤ ወሳኝ ነው፤ ቄብ ዶሮዎች በተገቢው እድሜ እንቁላል እንዲጥሉ ከመጀመሪያዉ ጨለማን በማለማመድ ከ 1 ወር እድሜ ጀምሮ እንቁላል እስከሚጀምሩ በጨለማ ውስጥ ማሳደርና እንቁላል መጣል ከጀመሩ በየደረጃው እስከ ምሽቱ 4 ሰአት ብርሀን መስጠት ያስፈልጋል፤ የዘር እንቁላል ጣይ ዶሮዎች ከ9-12 በሙቶ አውራዎችን እንደዝርያው ሁኔታ ማካተት ያስፈልጋል፤ በእንቁላል ምርት አሰባሰብ እንቁላል በቀን 4 ጊዜ ያህል በመሰብሰብ /በኩስ እንዳይበከልና እንዳይሰነጠቅ/ በቀዝቃዛ ቦታ ማጠራቀም ያስፈልጋል፤የሚታቀፍ እንቁላል ከ1 ሳምንት በላይ ሳይቆይ ቢታቀፍ መፈልፈል ላይ በጎ ተጽእኖ ይኖረዋል፤ እንቁላል ለማሳቀፍ ቆሻሻ ያልሆነ፤ ስንጥቅ የሌለው መካከለኛ ክብደት ያለው ሻካራ ያልሆነ ንጽህናው እየታየ መረጣ ይከናወናል ፡፡

የዶሮ በሽታ

በአገራችን ውስጥ አደገኛ ከተባሉ የዶሮ በሽታዎች ፈንግል፤ጉምቦሮ፤ሳልሞኔላ፤የዶሮ ፈንጣጣ፤ የሚጠቀሱ ሲሆን ክትባቶቹ በአገር ውስጥ ተመርተው ስለሚቀርቡ/ደብረዘይት/ በመጠቀም መከላከል ለምርት እድገት ወሳኝ ይሆናል፡፡ በአርሶ አደር አካባቢ የፈንግል በሽታ ክትባት የመጠቀም ልምድ ያለ ሲሆን በርካታ ዶሮዎችን ለሚያረቡ አርቢዎች የጉምቦሮ ክትባት

ጭምር መጠቀሙ ይመከራል፤ ኮክሲዲዮሲሲ የውስጥ ጥገኛ በሽታ ሲሆን መከላከያ መድህኒት መጠቀም ይቻላል፡፡

የፈንግል በሽታ /Newcastle /አደገኝነት አኳያ ክትባት የመስጠት ልምድ እየዳበረ ሲሆን የአጠቃቀም ፕሮግራሙ መጀመሪያ ሳምንት/3-7 ቀናት/ ሁለተኛው ከ 18-21 ቀናት፤3ተኛው 42-49 ቀናት፤በ14ኛው ሳምንትና ለእናቶች በየ 3ወሩ የሚሰጥ ሆኖ እንደየአካባቢው ባለሙያዎችን ማማከሩ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ባዮሴክዩሪቲ /Biosecurity/-- በሽታ ጀርም እንዳይገባም እንዳይሰራጭም የመከላከልና የመቆጣጠር ስርአት ነው፤

- በእርባታው አካባቢየውስጥ አያያዝ/ እጅ በሳሙና በመታጠብ ንጽህና መጠበቅ ፤ ቤቱን ማናፈስ፤እርጠበት መከላከል.../
- ጎብኚዎችን መገደብ
- ሌሎች እንስሳት ዝውውር በግቢው መከልከል /ድመት ውሻ.../
- የሞቱ ዶሮዎችን መቅበር/ማቃጠል፤
- ተንከባካቢው ጫማና ቱታ ቀይሮ መግባት አለበት፡፡
- ክትባት መስጠት

በአጠቃላይ ከዶሮ እርባታ ተግባር አግባብ ያለው ምርት ለማምረት ኋላ ቀር ከሆነው አረባብ ወደተሻሻለ /Semi- intensive/ ለማሻገር ጥረት በማድረግ በአያያዝ በአመጋገብ በጤና አጠባበቅ ላይ ክትትልና በቂ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡